# እኛም አቶ ሀጎስ አለን

**ከአቶ ልሳኑ - ዘብሄረ ደንቢያ**

ከዚህ በፊት ስለኢትዮጵያ ንጉሦች ተኮላ ሀጎስ ሲጽፍ እነ አፄ ቴዎደወሮስን እነ አፄ ሚኒሊክን ምን ያህል አጥፊና በታሪክ ተጠያቂ እንደሆኑ ሬሳቸው ከመቃብር ወጥቶ ለፍርድ መቅረብ ያለባቸው ሂትለሮች እንደሆኑ አድርጎ እንዳቀረባቸው የምንረሳው ሀቅ አይደለም፤ በአንፃሩ ኢትዮጵያ የነበራት ንጉሥ አፄ ዮሀንስ ብቻ እንደነበረና እርሱንም ቅዱስ ዮሀንስ አርጎ እንዳቀረበው እናውቃለን፤

ይባስ ብሎ አሁን ደግሞ አማራ ነኝ ብሎ የተነሳው አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ የአማራ ሕዝብ ከራሱ ብሄር ይልቅ ኢትዮጵያዊነቱን ከራሱ ጥቅም ይልቅ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም በማለቱ ያለፉት ነገሥታትም እነ ቴዎድሮስ፤እነ ሚኒሊክ የአማራ ብሄረተኝነቱን እንዲገፉ ባለማድረጋቸው ተወቅሽና ተነቃሽ ሆነው ለውግዘት በቅተዋል እኛም ሀጎስ አለን የምንለው ለዚህ ነው፤

“የአማራ ሕዝብ ከዬት ወዴት” በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ አ/አ ሰኔ 1985 በመጽሐፍ ደረጃ የወጣው ለምርምር የሚቀርብ የሥነ ጽሁፍ ይዘትና ውበት ኖሮት ሊተችበት የሚገባ ወረቀት አይደለም፤ በፖለቲካ አቀራረቡ ግን ከዚህ ጽሁፍ ያላነሱ የTPLF, የOLF ወዘተ. ጽሁፎች ቀደም ሲል የእያንዳንዳቸው ብሄር የተለዬ ባህሪንና ጡንቻን ለማሳየት ደረሰብን የሚሉትን ግፍ ለማመሳከር ይረዳ ዘንድ ታሪክ ያላወቀውን የኤርትራ፤ የትግራይ ፤ የኦሮሞ ታሪክ ወዘተ. በየጊዜው ሲተርኩልን እንደነበረ የምናውቀው ነው፤ለነገሩማ ወያኔም በጊዜው ጥያቄዬ የብሄር ሳይሆን የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው ብላ አውጇ እንደነበር ታሪኳ የሚዘክረው ነው፣ ኤርትራውያኖችም የቅኝ ግዛት ብለው እንዳነሱት ሁሉ ትግራዮችም እንደደገሙት ኦሮሞዎችም ሰልሰውታል፣ ስለዚህ በመንፈስ አንድም ሶስትም ናቸውና አቶ እንዳልካቸውም ወደዚያው ለመንፈስ እየተንደረደሩ ናቸው፣ ችግሩ የአማራውን ብሄርተኛነት እንደሚፈልጉት አጠናክረው የአቶ አንዳርጋቸው የአማራ ድርጅት ከኢትዮጵያ ቅኝ ግዝት ነፃ ለመውጣት ብሎ ቢነሳ አቶ አንዳርጋቸው አማራ ነፃነቱን ከየትኛው ኢትዮጵያ እንደሚጠይቅ ግራ ይገባናል፣ ምክንያቱም አቶ አንዳርጋቸው አማራውን ኢትዮጵያዊነቱን እንዲረሳ ይፈልጋሉና፣

አቶ አንዳርጋቸው ጽጌም “ከማን አንሼ” ብለው የተነሱና “የአማራው ሕዝብስ ከዬት ወዴት” በሚለው ጽሁፋቸው “አስናቀው ሻቢያ” ወይም “እኔ እበልጥ ወያኔ” ለመሆን የተነሱ ይመስላል፤ ይህን ካልን ዘንዳ የጽሁፉ ይዘት ምንድነው?

ገጽ 4 ምዕራፍ 4…የጽሁፉ ዋና ማቀንቀኛ መሰረተ ሀሳብ ነው፤ በአጭሩ “…በከፍተኛ ደረጃ የተደራጁ የተለያዩ የብሔር የፖለቲካ ድርጅቶች አሉ፤” እነዚህ ድርጅቶች ከብሄራዊ ጥቅማቸው በመነሳት የተለያዩ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎችን መንደፍ የሚያስችል አቅም አላቸው፤ ይህ አቅም ብሄረተኝነትን ነዳጅ አድርጎ በየጊዜው እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ አይሄድም፤እነዚህን የመሰሉ ጠንካራ ድርጅቶች ያሏቸው ሕዝቦችና በዚህ መንገድ ባለመደራጀቱ እንደተበተነ ያለው የአማራ ሕዝብ በአንድነት እንኳዝ ቢሉ የጉዞው አላማ ሺህ ጊዜ ቀና ቢመስል ጉዞው ከጎታችነትና ከተጎታችነት፣ ከፊት ቀዳሚነትና ከኋላ ተከታይነት ውጭ ነፃና እኩል ጉዞ መሆን አይችልም፣

ይህን ጽንሰ ሀሳብ በመያዝ የአማራው ሕዝብ በብሄር ደረጃ በተጠናከረ መንገድ ካልተደራጀ ከችግር እንደማይወጣ ወደኋላ እንደሚቀር ኢትዮጵያዊ ነኝ ማለቱም ቂልነትና መደናበር እንደሆነ ይህም እነ አፄ ቴዎድሮስንና እነ አፄ ሚኒሊክ የጫኑበት በሽታ በመሆኑ ኢትዮጵያ የሚለውን የጋርዮሽ ስሙን ተወት አርጎ ወደኋላ በመንሸራተት አማራ አማራ ነኝ ብሎ መዘመር እንዳለበት የሚገፋ አስተሳሰብ ነው፣

በጣም ዝቅ ያለውና የዘቀጠበት ቦታ ቢኖር ከሁለት ብሄሮች ስነሚወለዱና ስለሚኖራቸው ጠባይ አመለካከት በሕዝብ ትግልና እሮሮ ስለሚኖራቸው አቋምና ታማኝነት

“አድርባይነት” በሚል አስቀምጦ የሚሰጠው ትንታኔ ከፀረ ሕዝብ ከበታኝነት ሚና አያወጣውም (ገጽ 17-18) ያንብቡ፣ እነዚህ ግለሰቦች አባታቸው ኦሮሞ እናታቸው አማራ አያታቸው ትግሬ እሚታቸው ጉሙዝ ሊሆን ይችላል፣ ኢትዮጵያዊነታቸው ለምን አፀያፊ ይሆናል? ኢትዮጵያዊ ነኝ በማለታቸው ከኦሮሞ አባታቸው ተነስተው ኦሮሞ ነኝ ቢሉና ኦነግ ውስጥ ገብተው እንታገላለን ቢሉ ሀጢአቱ ምንድነው? ወይም ከአማራዋ እናታቸው ተነስተው ወደ አማራው አስተሳሰብ በመሄድ ከአማራነቱ ይልቅ ኢትዮጵያዊነቱ ስለሚያንገበግበው ኢትዮጵያዊ ነኝ ቢሉ ሀጢአቱ ምንድነው?

ኢትዮጵያዊ ነኝ ማለት ኋላ ቀርነት ነውን?

ይህን ሀሳብ በሰፊ ካቀነቀኑ በኋላ የኛው ሀጎስ በመጨረሻው ገፃቸው ላይ “ዶሮን ሲደልሏት በመጫኛ ጣሏት” እንዲሉ አርጎ አማራውን በመጀመሪያ ገፃቸው እንዳልጨፈጨፉት ኋላ ቀር እንዳላሉት ሁሉ በመጨረሻ አምድ ላይ ጀርባውን አሸት አሸት በማረግ አይዞህ ማሙሽ ጎበዝ ልጅ ነህ እነ አፄ አወናብደውህ ነው አማራነትህም አልተረሳም አሁንም በአማራነትህ ተሰብሰብ፣ የአርሶ አደሩን አሰባሰብ ታሪካዊ ግዴታው በአማራው ምሁር ላይ ይወድቃል ብሎ ነው የሚደመድመው፣

በአሁኑ ሰዓት ሕዝባችንን እርስ በርሱ ለማጋጨት ኢትዮጵያን ለመበታተንና እንደሐገርም እንደሕዝብም እንዳይኖር እነሻቢያ ከ1960 ዓም ጀምረው የተከሉትን መርዝ አሁንም ወያኔ፣ ኦነግ ወዘተ. በሚገፉበት ሰዓት ከማን አንሼው የኛው አቶ ሀጎስ ይህን ይዞልን መቅረቡ ብቻ ሳይሆን በትረ ሙሴውን ለመጨበጥ ሲሯሯጡ ዝም ብለን አናያቸውም፣

ዛሬ ተቃዋሚ ነኝ ብለው በቅንጅት ውስጥ ተሰግስገው አልፎም አመራሩን ጨብጠው በእስር ቤት ያሉትን እውነተኛ መሪዎቻችንን ገሸሽ ማረግ ብቻ አይደለም መፈንቅለ ድርጅት በማድረግ እምነታቸውን እሙን ለማድረግ በኦነግ ለመመራት ተስማምተው መግባታቸው ፈጽሞ አይገርመንም ከወያኔ ጋርም ተስማምተው የአዲስ አበባ ከተማን በሶስተኛ ደረጃ የእቁባይና የህላዊ ተቀጽላ ሁነው እንዳገለገሉ ይህ ጽሁፋቸው ለሹመት እጅ መንሻ እንደሆነ መረዳት አይሳነንም፣ ለወያኔ አገልግሎት መጨረሳቸውን በውል ባናውቅም ለሻቢያና ለኦነግ እየሰሩ መሆኑን እያየነው ነው፣

ይህን ጽሁፍ ላቀረቡልን ከልብ እናመሰግናለን

አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በራሳቸው አንደበት በይፋ ወጥተው መግለጫ እንደሚሰጡበት ተስፋ እናደርጋለን፣

በዚህ አጋጣሚ “የወያኔ ደጋፊ” “በታኝ” “ፀረ ቅንጅት” ብሎ ዋናውን ጥያቄ ከመመለስ ገሸሽ ማለት ፀረ ኢትዮጵያዊነት ነው፣ የቅንጅት ደጋፊ ነን የቅንጅት አመራር ነን በሚል ቅንጅት እኛ የምናውቀውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምጽ የሰጠበትን ድርጅት በስሙ የሚሸቅጡንና በውስጡ ሆነው በእውነተኛው አመራር ላይ መፈንቅለ ድርጅት ያረጉትን በጥብቅ መቃወምና ማጋለጥ በቅንጅት ላይ የደረሰበት አደጋ ለመመከት መነሳት እውነተኛ ኢትዮጵያዊነት መሆኑን መረዳት አለብን፣

ቅንጅት እያልን በጅምላ ከመፃፍ ከመናገር መቆጠብ አለብን እውነተኛው የቅንጅት አመራር ነን የሚሉ ፈንቃዮች (የሰሜን አሜሪካ መፈንቅለ ድርጅት) ቅንጅት እንዳልሆኑና በቅንጅትም ላይ ኪሳራ የጣሉ ነጋዴዎች ሽቶ የሚረጩ መስለው ቅንጅትን በተርብ እያስነደፉ መሆኑን መገንዘብ ያሻል፣ የቅንጅትን ህልውና ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ህልውና ዘላለማዊ ዋስትና ኢንሹራንስ የሆነውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምጽ አብልጦ ለሰጠ የራሳቸውን ጥቅምና ትርፍ ላመጣ በአለም ዙሪያ እየቸረቸሩት ነው፣

መርሳት የሌለብን አንድ ነገር አለ፣ ትግላችንን የሚያኮላሹት ሻቢያና አሜሪካን ብቻ አይደሉም በውስጣቸው ያሉት የጠላት መሣሪያዎች ጭምር ናቸው፣

**የተባበረ ትግላችን በአንድነታችን ግብ ይመታል!!**
**ከሀዲዎች ይጋለጣሉ!!**